## ***ሀላፊነት የጎደላቸው ምሁሮች ዕልቂት ያመጣሉ፤ ሀገር ያጠፋሉ !***

***መለስ ዜናዊ የእሱ መሰል ዘረኛ ምሁሮች ሀገርን አዋርደው ሕዝብን እንዳላስለቀሱ ሁሉ በሀገራችን የርዋንዳን ዕልቂት ሊያመጡ ይከጅላሉ ብሎ በሀገር ወዳድ ድርጅቶች ላይ ያላዝናል፡ ፡ አባቱ ዜናዊም ወያኔ ከወደቀ የትግሬ ተወላጅ ሁሉ ይጨፈጨፋል ብዬ እሰጋለሁ በሚል እሳት ካየው ምን ለየው ዘረኝነትን ሲያሰሙ ነበር። የርዋንዳ ዕልቂትን የጠነሰሱና ያፋፋሙ የሁቱ ጎሳ ዘረኞች ነበሩ ። እነዚህ መለስና ስብሐት ነጋን መሰል የሁቱ ምሁር ተብዬዎችራዲዮ ሚል ኮሊን ወይም የሺ ተራሮች ራዲዮ የሚል አቋቁመው ፀያፍ በሆነ ቋንቋና ይዘት ቱተሲ ጎሳ አባላትን ጨፍጭፉ ፤  ወደመጡበት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ሬሳቸውን ወደ ወንዝ ጣሉ፤ ቱትሲዎች በረሮ ናቸው ወዘተ በሚል ሰፊ ቅስቀሳ አካሂደው ሕዝብን እርስ በርሱ አጫርሰዋል። ከሶማሌ የጦር አበጋዞች በስተጀርባ ምሁር ነን ያሉ ጎጠኞች ነበሩ፤ ዛሬም አሉ። የአረብ ሀገር አክራሪዎች ፤ የታሊባንና አለ ሸባብ ሰው አራጆች፤ የአውሮጳ ናዚዎችና ፋሺስቶች፤ የአፍሪካ አማፅያን ተብ ዬዎች ወዘተ መሰረታቸውና የሚቃኟቸው ምሁራን ናቸው። የወያኔና የመሰሎቹ የጥበትና ዘረኝነ ት በሽታ የሕዝብ ሳይሆን በጥላቻ ያበዱ ጥቅም አሳዳጅ ንዑስ ከበርቴዎች ወይም ምሁሮች መሆኑም የታየ ነው።***

***በሀገራችን የምሁሮች ፈር ቀዳጅነትና ለለውጥ ታጋይነት በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴም ሆነ በኢሕአፓ በተደጋጋሚ የተረጋገጠ ነው። ከዚያ በፊት ካልንም የኢትዮጵያ ምሁሮች የጣሊያ ን ወረራ ተቃውመው ባደረጉት ተጋድሎ በብዛት በጨካኝ ፋሺስቶች ተገድለዋል። አርበኞች እንደነበሩ ሁሉ እንደ መለስ ዜናዊ አያት ዓይነት አሳፋሪ ባንዶች ነበሩና ምሁሮችለሕዝብና ለሀገ ር ቆመው ቢታገሉም ለጥቅማቸው ሲሉ ለጠላት የተጎነበሱ፤ ባንዳ የሆኑና ሀገርን የከዱም ጥቂቶ ች አልነበሩም። ወያኔ በባዕዳን ሙሉ ድጋፍ ለስልጣን ሲበቃ ወግድ ብለው የተሰለፉ ተማሪዎች፤ እምቢ ለዘረኛ አንገዛም ብለው ሕይወት የገበሩ ኢሕአፓዎች የነበሩ ቢሆንም ከዚያ በላይ ደግሞ ምሁሩ በሀገርም በባዕድ ሀገር ሆኖ ለወያኔ ማጫፈሩ መሸፋፈን የሌለበት ሀቅ ነው። እነ እንድርያ ስ እሸቴና ዛሬ ተቃዋሚ ነን ሊሉ የተነሱ ምሁሮች ሎንዶን ድረስ ሄደው መለስን ሀይ ሀይ እያሉ ማጀባቸውን የምንረሳው ሊሆን አይገባም። መለስ አዲሰ አበባ ሲገባም በቴሌቪዥን ክርክር በሚል ሽፋን የሰጡና ሕዝብን ሊያደናግሩ የተነሱ እነማን አንደነበሩም ሕዝብ አይረሳም።  የሽግ ግር ጉባዔ ብሎም ዘረኝነትና ግንጠላን ሊያፀድቅ ሲነሳ ያጀቡትንና ያጨበጨቡ ምሁሮች  (ዛሬ ተቃዋሚ ነን ቢሉም አንዳንዶቹ) ማስታወስም እንችላለን ። ይህ የሰፈነ አድር ባይነት ከመብዛቱ  የተነሳ በዚያ ጉባዔ የወያኔን ሻጥር አልቀበልም ያሉትን ፕሮፌሰር አስራትን ውሎ አድሮ በሕዝ ብ ዘንድ የሚደነቁ አድርጓቸዋል። ትክክልም ነበር መደነቃቸው ። እጅ የሰጠው ምሁር ክፍል የወያኔን ከፋፋይ ቅስቀሳና ድርጊት አጅቦ ለወያኔ መሰሪ ተንኮል ሰለባ ሆኖ ትግልን ጎድቷል። ለወያኔ በብዕር ኩሊነትም ያገለገሉና ሀሰትን የፃፉ ነበሩ ።  ሕዝባችን ጦርነት ሰለቸው የሚለውን***

የወያኔ ልፈፋ ተቀብለው ያስተጋቡና ለጦረኛው ወያኔ ጊዜ እንስጠውን የሰበኩ ምሁሮች ጥቂት አልነበሩም። ሌሎች ደግሞ የወያኔ ሹመኛ ሆነው ሀገርን በድለዋል። ዘረኛ ምሁሮች ወያኔን እጅ በው አርባጉጉና በደኖን ወልደዋል። ኢትዮጵያዊነትን እንደራደር ያሉ፤ በአማራው ሕዝብ ላይ እጅ አጅ የሚል የጥላቻ ቅስቃሳ ያካሄዱ፤ የዚህኑ ሕዝብ ፍጅት የቀሰቀሱ፤ በዚህ ሕዘብ ላይ ተነሱ ብለው መፅሀፍ የፃፉ ወዘተ አርሶ አደሮች ሳይሆኑ ዶክተር በሉን ምሁር በሉን ያሉት ናቸ ው። በወያኔ ላይ ከጠዋቱ ሕዝባዊ ትግልን ለማደራጀት ይደረግ ለነበረው ጥረት እንቅፋትና ጋሬ ጣ የሆኑትም ምሁሮች ለመሆናቸው ክርክር አያሻውም ። እነዚህ ክፍሎች አደብ እንዲገዙ፤ እን ዲነቁ የተደረገው ትግል ጊዜ ፈጅቷል። ትላንት መለስን ልጄ ያሉ ዛሬ መለስ ጨቋኝ ነው እስኪ ሉ ድረስ ማለት ነው። ከመጀመሪያው የወያኔን ጠላትነት አውቀው መስዋዕትነት ለከፈሉት ክብርና ምስጋና ሲገባ ዛሬ የተያዘው ፈሊጥ ተሳስተን ወያኔን ደግፈን ነበር ብሎ ይቅርታ መጠየ ቅ ሳይሆን ሲታገሉ የቆዩትን ማውገዝናእስከ ትላንት ወይኖ ወይም ከመለስ ጫማ ስር ተደፍቶ (አንዳንዴም ወንጀል በሕዝብ ላይ የፈፀመውን) የነበረውን ጀግናና መሪ ብሎ ማዳነቅ ሆኗል ። ይህ ደግሞ ስልጡን ፖለቲካ መስሏቸው በይፋ የሚደነፉም አሉ ። ይህን የኢትዮጵያ ምፀትና ሸከም  የሚያንፀባርቀው ምሁር የተባለው መሆኑም ሊታወቅና ሊታመንበት ይገባል።

እያንዳንዱ ምሁር ቆም ብሎ ፤ ዞር ብሎ በ1981 አቅዋሜ ምን ነበር? ከዚያስ በኋላ ብሎ ቢጠይቅና በዚያን ጊዜ በርግጥም ተሳስተን ነበር፤ የለንደኑ ጉባዔ ሲወገዝ ሄደን መለስን መደገፋችን ፍፁም ስህተት ነበር፡ ተማሪዎች ተሰልፈው ሲገደሉና እነ ኢሕአፓ ሲጨፈጨፉ ዝም ማለታችን ስህተት ነበር ፤ ለወያኔ መሳሪያ መሆናችንነ ጠፋት ነበር ብሎ ማመን ለትግሉ መስመር መያዝ አንድ እርምጃ ወደፊት በሆነ ነበር። ፕሮፌሰር አስራት የግንጠላና የዘረኛ ውሳኔ ን ሲቃወሙ እሳቸውን በመደገፍ ፈንታ ለፀረ ኢትዮጵያው ወያኔ ማጨብጨባችን ጥፋት ነበር ያሉ በነበሩ ከዚያ ስህተት ትምህርት ተወስዶ ሌሎች ተመሳሳይ ስህተቶች ባልተደገሙ ነበር ። ነበርን ነበር ይወልደዋል ነውና በአማራው ሕዝብ ላይ ያ ሁሉ የጥላቻ ዘመቻ ሲካሄድ ፈታውራሪ ሆነው ያጓሩት ጥፋታቸውን አምነው በነበር ምንኛ ፀረ ወያኔው ትግል በተጠናከረ ነበር።  ይህ ግን አልሆነም። ወያኔን የደገፈወና ጥንካሬና ጊዜን የሰጠው ምሁር ወይ በጥፋቱ ቀጠለበት ወይ ም ከመ ቅፅበት ተቃዋሚ ነኝ ብሉ ራሱን ሰይሞ አንዲትም የፀፀት ድምፅ ሳያሰማ የሕዝብን ትግል ተደባለቅሁ ብሎ አዘባረቀው። ዛሬ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪ ነን የሚሉ ሁሉም ከወያኔ ጋር ምንም ያልተነካካ ታሪክ አላቸው ማለት አለመቻላችን የሕዝቡ ትግል ደካማ ጎን ኖኖ ቀጥሏል። ትግሉ ተራዘመ ወዘተ በሚል ወያኔን ሲታገሉና መስዋዕትነት ሲከፍሉ የቆዩትን ድርጅቶች የሚተቹ ራሳቸውም ሆኑ የሚመሯቸው ለወያኔ መሳሪያ ሆነው የቆዩ መሆናቸውን ማወቃቸውና መቀበላቸው ተገቢ ነው። ለምን የወያኔ ዕድሜ ተራዘመ? ለወያኔ ያደረው ፤ በወያኔ የሚወናበደው፤ ለወያኔ ጊዜ እንስጠው የሚለው፡ ሕዝብን ሲበድል ከርሞ የሕዝብ መሪ ነኝ የሚ ለውና ድከመቱን ስህተቱን ማንመ ያቃተው ምሁር በመብዛቱ ነው። ይህን ሀቅ ሲነገረው ፀረ

ምሁር ናችሁ ብሎ ማውገዝ የሚቀናው ስህተቱን ማመንና ማረም ያቃተው ምሁር በፖለቲካው መድረክ በመብዛቱ ነው:: ራሱን ምሁር ቢልም ሀገር ወዳድ ምሁር መሆን ያቃተው ፈሪሳዊ ምሁር አዋቂ ነኝ ብሎ በመሰየሙ ነው::

ዛሬ ወያኔ ምሁሮችን በሀገር ቤት በብሔርና ሀይማኖት ከፋፍሎ ማንም አይነካኝም ብሎ እንደሚ ፎክረው ሁሉ በባዕድ ሀገሮችም ይኸው ክፍፍል በወያኔና በሌሎች ጠባብ ክፍሎች እየተራገበ ሰፍኖ ይገኛል:: ይህም የአንድነት ሀይሎችን ትግል እያደናቀፈ መሆኑ ክርክርን አይጠይቅም:: የሌባ ዓይነ ደረቅ እንዲሉ የዚህ ዓይነቱ አይጠቅሜ ምሁር ዋና ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉት ይባስ ብለው የአንድነት ሀይል የሚባል የለም ብለው ሲያንቋሽሹም ተደምጠዋል:: ዛሬ ይህን ጉዳይ ለማንሳት ምክንያት የሆኑን ክስተቶች አንድም ከተገንጣይ ሰፈር ምሁሮች እየተሰማ ያለው አደገኛ የጥላቻ ልፈፋ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ብልግና ደረጃ በደረሱ የኢንተርኔት የውይይት ተብዬ መድረኮች ላይ እየተሰማ ያለው ሕዝብን የመዘለፍና የማዋረድና የማቃረን አዲስ ዘመቻ ነው:: ይህ ነው የርዋንዳውን የ ሺ ኮረፍታ ወይም ተራራዎች ራዲዮን (ራዲዮ ሚል ኮሊንስን) ዘመቻ ሊደግም የተነሳው:: ወያኔ በዚህ ሀላፊነት በጎደላቸውግን ራሳቸውን የተማረ ያወቀ ምሁር በሚሉ ጭቅጭቅና ሕዝብን መስደብ ዝቅጠት ውስጥ ገብቶ የርሰ በርሰ ጥላቻን እያራገበና ክፍፍልን እያጧጧፈ ነው:: አማራውና ኦሮሞው በተለይ እርስ በርሱ፣ ክርስቲያኑና እስላሙ እርስ በርሱ እንዲጫረስ ወያኔዎች ተሸፋፍነውና ተቃዋሚ መስለው እየሰበኩ መሆናቸው ን ማወቅ ከባድ አይደለም:: ለዚሁ ሰለባ ሆነው ፀያፍ ዘመቻን በብሄረሰብና ሀይማኖት ደረጃ የከ ፈቱት ምሁራን ወይም ሀቀኛ ኢትዮጵያዊ ሳይሆኑ ለሀገራችን ሸክሞች፣ መርገሞችና አደጋዎቸ ናቸው:: ይህ ዕልቂትን ጋባዥና ሀገርን አጥፊ ዘመቻና ልፈፋ መቆም አለበት፣ወይም እንዲቆም መደረግ አለበት:: ዛሬም እንደትላንቱ ሀገር ወዳጹ ምሁር ከተደናገረና ቦታውን አስመሳዮቹና ዘረኞቹ ከወሰዱ ሕዝብ ለባሰ መከራ መጋለጡ የማይቀር ይሆናል::

ኢሕአፓ የምሁሩን ድርሻና ሚና ሲያስረዳ በመሰስከረም 1983 (ዴሞክራሲያ ቅፅ 16፣ ቁጥር4) የሚከተለውን አስፍሮ አንደነበር መጥቀሱ ጠቃሚ ይሆናል፤

*“ ተቃውሞን ማሰማት፣ ተበደልኩ ብሎ ማንገራገር፣ እንዴት! ብሎ ስልጣናትን መሟገት ፣የሚ ፈታተኑ ሐሳቦችን መሰንዘር በማይታለምባት ፤ ሥርዓተ ትምህርቱም ለሥርዓቱ በሚያረግድባት ፊውዳላዊ ኢትዮጵያ ተማሪውና ተራማጁ ምሁሩ የላብ አደሩን ፤ የአርሶ አደሩን፣ ባጠቃላይም የሰፊውን ሕዝብ ብሶት በማስተጋባት ፤ ጥያቄዎቹን በማሰማት ከተማሪና ከሙያ ማህበራት አቅም በላይ በመንጠራራት የግፉዓን ጠበቃም፣ ሐዋርያም፣ሰማዕትም ሁኖ የፈፀመውን ገድልና ለየካቲት አብዮት ያነጠፈው ጥርጊያ፣ አብዮቱም ከሕዝብ እጅ እንዳያፈተልክ የአብዮት ጠር ሁነው ከች ካለት ፋሺስታዊያን ሀይላት ጋር ያደረገው ግብግና የከፈለውምዋጋ በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ውስጥ ራሱን የቻለ በነድ የተፃፈ ምዕራፍ የያዘ ነው ::”*

በዚህ መልክ ነበር ኢሕአፓ የምሁሩን ሚናና ሀላፊነት የገለፀው ። የምሁሩን ሀላፊነት በተመለከተ ተም የሚከተለውን አስፍሮ ነበር፤

*“ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ብዙ ውጣ ውረድን ያለፈ፤ ብዙም ገና የሚጠብቀው እንደመሆኑ መጠን ከታጋዩ፤ ከአገር ወዳዱ የሚጠበቀው ደግሞ በዚያው ልክ የበዛ ነው። በተለይ የኢትዮጵያ ምሁር--ተማሪ በቀላሉ ተከፍሎ የማያልቅ ዕዳ እንዳለበትም ላንዳፍታም መዘንጋት የለበትም። ያ ታርዞ ያለበሰ፤ ተርቦ ያበላ ፤ አንጅቱን አጥፎ አፈር ገፍቶ ሀገርን ሀገር ያሰኘ፤ በመሐይምነት ተወስኖ የትምህርትን በረከት ያደለ ፤ ጠበብትና ሊቃውንትን ያስገኘ ፤ ጎስቋላ ሕዝብ ፤ ያ ብሶት ዋይታው የወለደውን ፤ ጅግኖች ልጆቹ የረገፉበትን አብዮት ተነጥቆ፤ እግር ተወርች ታስሮ፤ አፉን እንደገኛ ተሸብቦ ፋሺስታዊ ደይን ሕዝብ የሚማቅቅ ሕዝብ ከምሁራን ልጆቹ ብድሩን ይጠይቃል ። ጊዜው በተራዘመ ቁጥር ወለዱም ይጨምርና መክፈልም ያዳግት ይሆናል ። ሆነም ቀረም ምሁር--ተማሪው፤ አገር ወዳዱ የህሊና ዳኝነት የሚበይንበትን ሁሉ መክፈል ያለበት ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ዕብሪት፤ ትምክህት፤ ጠባብ.ንት በተባሉ ችንካሮች ተቸንክሮ ኤሎሄ! ኤሎሄ! እያለ በሚያቃስትበትና የብተና ጻዕረ ሞት ጥላውን አጥልቶበት እንደ ሕዝብ አንድንቱን ጠብቆ፤ ኣንደሀገር ህለ ሆኖ መቀጠሉ እያጠራጠር በመጣበት ባሁኒቱ እኪት ሰዓት ነው ።*
*የተለያየውን አገናኝቶ፤ ተተሰበርውን ጠግኖ ፤የተሰነጠረውን አያይዞ፤ ያፈነገጠውን አስማምቶ፤ የተብተነውን ለቅሞ ፤ባጭር ቃልም ሀገርን በአዲስ መልክ የማስተናበር ገና በሩቁ የሚያስፈራ እጅግ ከባድ ዕዳና ሃላፊነት ነው። ሆኖም “ላይችል አይሰጠውም “ ይባላልና ይህንን ችሎት እውን ለማድረግ፤ ኢትዮጵያ ሀገሬ ናት ብሎ አፉን ሞልቶ የሚናገር ሁሉ ድርሻ ድርሻውን ለመሸከም አፈፍ ብሎ እነሆኝ የሚልበት ጊዜ ዛሬ ነው። “*

ኢሕአፓ ይህን ማሳሰቢያ ከሰጠ ሀያ አንድ ዓመታት ቢያልፉም ምክሩና ግንዛቤው ግን የዛሬ ናቸው። ከዚህም ቀጥሎ ምሁሩ በአጠቃላይና በተለይም በወቅቱ በባዕድ ሀገር ያሉት ምሁራን የነበራችውን ሚናም ዘርዝሮ እንደሚከተለው አቅርቦ ነበር ።

*“ መጽሐፉ እንዲህ ይላል፤ እንዲያ ያዛል፤ እንዲህ ይሰራለታል ፤ እንዲያ አይሰራለትም እየተባለ እንደ ቃለ እግዚያብሔር የሚነበነብበት፤እንደ በቀቀን የሚንጣጡበት፤ አሜን ያለ አማኝ ተብሎ ሞገስ የሚያገኝበት፤ የጠየቀ የመረመረ መናፍቅ ተብሎ ለኩነኔና ውርጅብኝ የሚዳረግበት የፖለቲካ ዘይቤ መዳረሻውን፤ ያስከተለውን መዘዝና ሰቆቃው ፤ ያፈለሰውን ሀገር ፤ ያነገለውን ንብረት አሁን መቼውም ጊዜ ይበልጥ ተመክሮ ቅልጥጥ አድርጎ ኣሳይቶናልና ወደዚያ ተመልሶ ዳግመኛ መዳከሩ ቢያንስ የሞኝ ፈሊጥ ይሆናል ። በጥራዝ ነጠቅነት መክነፍን፤ በሌጣ ትርጉም መጋለብን፤ እንዳፈተተ መቆንጸልን*

*ለማስቀረትና በዚህም ምክንያት የሚፈጠረውን የተሳከረ ሂደትና መመሳቀል ፈር፤ አቅጣጫ ለማስያዝ፤ ፖለቲካዊ ትንታኔዎች አየር ላይ መጥቀው በሕዝብ አናት ላይ የሚበሩ ሳይሆኑ ወረድ ብለው ከሕዝቡ ወዝ ጠረን ጋር እየተዛመዱ፤ የሕዋሳቱን ንዝረት የሚያሰሙ ፤ ስሜቱን በትክክል የሚተረጉሙ፤ ምኞቱን የሚያንጸባርቁ እንዲሆኑና የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ እድገት ደልዳላ መሰረት ላይ እንዲዋቀር ከማድረግ አኳያ የምሁሩ ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። "*

አለመታደል ሆና በአሁኑ ጊዜ በፖለቲካው መድረክ አለን አለን የሚሉት ምሁሮችና ምሁር ነን ባይ ጥራዝ ነጠቆች አደብ መግዛትን ሳይሆን መቧረቅን፤ የሕዝብን ፍላጎት ማወቅና ማክበር ሳይሆን በሕዝብ ላይ መጨፈርን፤ በትዕቢት መወጠርን፤ አንድነትን ሳይሆን ክፍፍልንና ዘረኝነትን ፤ የሚታገሉትን ማክበር መደገፍ ሳይሆን መዘርጠጥ ማጥቃትን ፤ ጀግንነትን ሳይሆን ብሩቁ ሆኖ የአፍ ታጋይነትን የመረጡ ይመስላሉ## ወዳለፈው የጭቆና ዘመንና ስርዓት መመለስ የማይቻል መሆኑ ግልጽ ሊሆን እንደሚገባው ሁሉ ኢትዮጵያን ቅርጫ ማስገባቱንም ሕዝብ እንደማይቀበል ማወቅ ያስፈልጋል ። ራሳችውን ልሂቅ ምሁር ብለው ሰይመው የተኩራሩ ግን ችሎታቸው የባዕድን ቀመርና ዕዝ (ያውም በጥራዝ ነጠቅነት) መገልበጥ መከተል ብቻ የሆኑ ግለሰቦችን ገለል ማድረጊያው ጊዜ ደርሷል --ግዴታም ነው። ሀገር ወዳድ ምሁሮችም የቀድሞዎቹ አኩሪ ምሁሮችንና ስንደቅና አላማ ተከትለው መድረኩን መረከብ አለባችው ። በዛሬው ዘመን ጽንፈኝነትን በሀይማኖትም ሆነ ብሄረሰብ ደረጃ የሚገፋ ጠባብና በጥላቻ የተሞላ ዜጋ ምሁር ሊባል አይችልም። በአንጻሩ ደግሞ በሀገር አንድነት ሽፋን የሌሎችን ስብዕናና መብት የሚጋፋና የሚጻረር ዜጋ በሀቅ ኢትዮጵያን አይወድም። ለጥላቻና ጠባብነት የወያኔ ሲብቃ ሳል ሌሎች በዚህ ተዘፍቀው ራሳችውንም አዋርደው ዕልቂት ባይጋብዙና ህግራችንንም ለጥፋት ለመዳረግ ባይቅብዘበዙ ይመረጣል ። የወያኔ አገዛዝ ሲያዘም ክርሞ ዛረ ሊውድቅ አንዲት ኤማም እንደቀረው ግልጽ ነውና ከወያኔስ ውድቅት በኋላ ምን የሚለው ጥያቄ የቅንጦት አይደለም ። የጥላቻ አባወራዎች ፤ ጥራዝ ነጠቆች፤ ባዕዳን ከነቅጥረኞቻቸው ነገን እንዳይቀሙን፤ በፈሰሰው ደማችን እንዳይቀልዱብን ጠንቅቀን መገኘት አለብን ። በሚዛኑ ላይ ያለችው ስንት ሰማዕት የወደቁላት ውድ ሀገራችን ናትና አጥፊዎች ይፈነጩ ዘንድ መቼም መፈቀድ የለበትም።

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ትከበራለች !
በጋራ ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንታግል !!